# <u>ሆያ ሆዬ</u>

ሆያ ሆዬ! ሆ!...ሆያ ሆዬ! ሆ!

መጣና ጌታችን
እንደልምዳችን ፡፡
ክፈት በለው ፤ በሩን
የምርጫውን ፡፡

ሆያ ሆዬ! ሆ!...ሆያ ሆዬ! ሆ!

እዚያ ማዶ ፤ ወንበር አለ
ያስቀምጣል ፤ ላልታገለ
ከፓርላማው ፤ አስቀምጡን
እናጨብጭብ ፤ ወንበር ስጡን
በትግል ሰበብ ፤ እንግባ ፤ መሃል
ካመረርንማ ፤ ይጨርሱናል
አጎንባሽ ፤ ቢሉህ ፤ አትስጠው ፤ ጆሮ
ጠላት ፤ ኃያል ነው ፤ ማን ይንካ ፤ ደፍሮ ፡፡

ሆይሾይ ፤ ሎሚታ
እስቲ ፤ እናምታታ ፡፡
ሆይሾይ ፤ ሎሚታ
እስቲ ፤ እናምታታ ፡፡

አጋፋሪ ፤ ሕብረት ፤ ፈጥሯል
ባከራሪዎች ፤ ተወጥሯል
እጅ ፤ እንዳንሰጥ ፤ ችግር ፤ ፈጥሯል
ያገለግላል ፤ ፈሪ ለጌታው
ለምን እንድከም ፤ ከንቱ ላንረታው
ቋጠሮው ከብዷል ፤ መቼም አንፈታው
ደከመን ፤ በቃ ፤ ብዙ ፤ ተለፋ
አትነካኩን ፤ ቆርጠናል ፤ ተስፋ ፡፡

መጣና ጌታችን
እንደልምዳችን ፡፡
ክፈት በለው ፤ በሩን
የምርጫውን
ክፈት በለው ፤ በሩን
ፓርላማውን ፡፡

አመት አውዳመት
ድገምና ፤ አመት
ድገምና ፡፡
የወያኔን ቤት ፤ ድገምና
አመት
ድገምና ፡፡
ባንዳ ፤ ይፍሰስበት
ድገምና
አመት
ድገምና ፡፡

ክበር በባንዳ ፤ ክበር በአንጃ
መከረምህን ፤ እንጃ
ክበር በባንዳ ፤ ክበር በአንጃ
መከረምህን ፤ እንጃ ፡፡